# የፎል (Fall) 2026 የትምህርት ምዝገባ የማመልከቻ ሂደት




## ማመልከቻዎን ይጀምሩ:- ከጁን 30 - ጁላይ 30፣ 2026

**የአመልካቾች የፍላጎት ማሳያ የመመዝገቢያ ቅጽን ይቀላቀሉ:–**
በፍላጎት ማሳያ የመመዝገቢያ ቅጽ ዝርዝሩ ውስጥ ለመካተት የQR ኮዱን ይቃኙ፤ መረጃዎን በማጋራትም ቀጣዩን ሂደት በጽሑፍ መልእክት ወይም በኢሜይል ይቀበሉ።

**የመመዘኛ ፈተና መውሰድ ይኖርብዎታል:–**
የመመዘኛ ፈተና መውሰድ ለመረጡት ፕሮግራም ብቁ መሆንዎን ለማረጋገጥ ይረዳናል::

## ቀጣይ ሂደቶች በትምህርት ፕሮግራም

### የሙያ ስልጠና

- የአመልካቾች የፍላጎት ማሳያ የመመዝገቢያ ቅጽ
- የመመዘኛ ፈተና
- ከመረጡት ትምህረት ጋር የተያያዘ ተጨማሪ ፈተናን መውሰድ
- ከፕሮግራሙ ሀላፊ ጋር የሚደረግ ውይይት
- እጣ

የምግብ ዝግጅት ጥበብ ትምህረት ለመውሰድ ተጨማሪ ፈተና አያስፈልግም

### የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና ለዜግነት ፈተና መዘጋጃ ትምህርት

- የአመልካቾች የፍላጎት ማሳያ የመመዝገቢያ ቅጽ
- የመመዘኛ ፈተና
- እጣ

ለዜግነት ፈተና መዘጋጃ ትምህርት ከፕሮግራሙ ሀላፊ ጋር የሚደረግ ውይይት ይኖራል

### GED በእንግሊዝኛና በስፓንሽ

- የአመልካቾች የፍላጎት ማሳያ የመመዝገቢያ ቅጽ
- የመመዘኛ ፈተና
- ከፕሮግራሙ ሀላፊ ጋር የሚደረግ ውይይት
- እጣ

### ኮምፒውተር እና ቴክኖጂሎጂ

- የአመልካቾች የፍላጎት ማሳያ የመመዝገቢያ ቅጽ
- የመመዘኛ ፈተና
- እጣ

ለአንዳንድ የኮምፒውተር እና የቴክኖሎጂ ትምህርቶች ተጨማሪ ፈተናን መውሰድ አለብዎት

## ማመልከቻውን ከጨረሱ በሁዋላ የሚኖረው ቀጣይ ሂደት

የዲሲ የቤት አድራሻዎን ማረጋገጫ ይዘው ከኦገስት 10 እስከ ኦገስት13፣ 2026 ባለው ጊዜ ውስጥ ሃርቫርድ መንገድ በሚገኝው ትምህር ት ቤታችን መምጣት አለብዎት::
የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ይዘው የመጡና የማመልከቻ ሂደቱን የጨረሱ አመልካቾች ወደ እጣው ውስጥ ይገባሉ::
እጣው ከወጣልዎት፣ የምዝገባ ሂደትዎን የሚያጠናቅቁበትን ሂደት እናሳውቅዎታለን።
1100 Harvard ST. NW, Washington, DC 20009

## እጣው የሚወጣበት ቀን:- አርብ ኦገስት 14፣ 2026 ነው::

**ሁሉንም የምዝገባ ሂደት ያሟሉ አመልካቾች አርብ ኦገስት 14፣ 2026 በሎተሪ ውስጥ ይካተታሉ::**

ቀጠሮ መያዝ አለብዎት
የአመልካቾች የፍላጎት ማሳያ የመመዝገቢያ ቅጽ ላይ አስፈላጊውን መረጃ ካስገቡ ቀጣዩን ሂደት እናሳውቅዎታለን

ለማንኛውም መረጃ በዚህ ኢሜል-soutreach@carlosrosario.org ይፃፉልን ወይም: 202 797 4700 ይደውሉ።